# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 3: «**የሌሊት ጀብዶች**»

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, ዳንኤልiel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: አቶ ሙላቱ INTERROGATED**

- **ፖሊስ ሙሉጌታ(M, 45)**
- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**

**SCENE2: ወ/ሮ ሉሊት AT THE አቶ መኩሪያS’**

- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **አቶ መኩሪያ (M, 45)**

**SCENE 3: ንጉሴ LOOKS FOR ምህረት**

- **ንጉሴ (M, 16)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **OLD SENILE WOMAN (F, 70)**

**SCENE 4: ምህረት VISITS ዳንኤል AT NIGHT**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

## INTRO

## 1. NARRATOR

**ሰላምታችን ይድረሳችሁ! ይህ «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል» የሚለው ክፍል ሶስት ድራማ ነው። የዛሬውን ጭውውት ከመጀመራችን በፊት እስቲ እስካሁን የነበረውን መለስ ብለን እንቃኝ። ምህረት ሙላቱ ከዳንኤል ጋ የግብረ ስጋ ግንኙነት ከፈፀመች በኋላ ማርገዟን አውቃለች። በዛ ላይ ዳንኤል ኋላፊነቱን በመካዱ የሆነውን በሙሉ ማመን አቅቷታል።**

## 2. EPISODE 1, LINES 9 – 10:

*ምህረት: ዳንኤል ማርገዜን ከነገርኩት ቀን አንስቶ አናግሮኝ አያውቅም።... ከዛ በፊት ግን አበድኩ ተቀበርኩልሽ ነበር የሚለኝ። ለምንድን ነው ይህን የሚያደርገው?*

*ትዕግስት: ምህረት፤ ባክሽ ሁሉም ወንዶች ናቸው ይህንን የሚሉት።*

## 3. NARRATOR:

**የክፍላቸው ልጅ ንጉሴ ጃለታ ስለሆነው ነገር ሁሉ የሚውቀው ነገር የለም። ምህረት አልፈልግህም ስትለውም እንደመፍትሄ እፅ እና ሌሎች መጥፎ ተግባራትን መጠቀም ጀምሯል:**

## *KW BEGIN*

## 4. EPISODE 1, LINES 66 – 67:

***ንጉሴ:*** **ርዕሰ መምህሯ ብታየኝ ምን የምታደርግ መሰለህ? ለዛውም ከ... ከ...**

***PEDDLER:*** **ምን? ከእፅ ነጋዴ ጋ? የኔን ጋንጃ ሳትከፍል ከማጨስህ በፊት ስለዚህ ልታስብበት ትችል ነበር።**

## *KW END*

**5. NARRATOR**:

**ይህ በእንዲህ ሳለ ሳለ የምህረት አባት አቶ ሙላቱ በፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል። አቶ ሙላቱ የንጉሴን ቤተሰብ በመዝረፍ ነው የተጠረጠሩት። በዛ ላይ አቶ መኩሪያ ከተባሉ ሰው ጋ ሌላ የሚጋሩት ምስጢር ያላቸው ይመስላል:**

**6. SEASON 1, EPISODE 7, LINES 28-29**

*አቶ መኩሪያ: ጥሩ! - ይኼውልህ ገንዘብህ ። 40,000 አዲስ የባንክ ገንዘብ፤ ከፈለክ መቁጠር ትችላለህ።*

*አቶ ሙላቱ: አያስፈልግም አምንሀለሁ። መኩሪያ። ይሔውልሀ- ከእንግዲህ ህፃኗ ያንተ ናት።*

**7. NARRATOR:**

**የዛሬው ጭውውት «የሌሊቱ ጆብዶች» የሚል ነው። አቶ ሙላቱ ፖሊስ ጣቢያ ሆነው ቃል ሲሰጡ እንስማ።**

**<u>SCENE 1: አቶ ሙላቱ INTERROGATED</u>**

**8. ATMO: POLICE STATION**

**9. አቶ ሙላቱ:** **ፖሊስ ነገርኩዎ እኮ! ጃለታ ሲዘረፍ እኔ እሱ ጋር መስራት አቁሜ ነበር።**

**10. OFFICER ፖሊስ ሙሉጌታ:** **በትክክል ይህን እኮ ነው የምለው አቶ ሙላቱ። እርሶ ስራውን እንደለቀቁ ምንም ያህል ቀናት ሳይቆጠሩ የአለቃዎ ቤት ተዘረፈ። (ironically) እንዴት ያለ አጋጣሚው ነው! ከዛ ከለቀቁ በኋላ ሌላ ስራ አግኝተዋል?**

**11.** አቶ ሙላቱ: አላገኘሁም።

**12.** ፖሊስ ሙሉጌታ: ስንት ልጆች አለዎት?

**13.** አቶ ሙላቱ: **(hesitates)** ሶስት።

**14.** ፖሊስ ሙሉጌታ: አዩ! ሶስት ልጆች እርሶ እና ባለቤትዎ ሲጨመሩ … አምስት ሰዎች ፣ ለዛውም በከተማ ኑሮ! ይህ ሁላ ሰው የሚበላው እና የሚለብሰው ይፈልጋል። **(sternly)** ስራ ሳይኖርዎ ታድያ እንዴት ብለው ነው ቤተሰብዎን የሚያስተዳድሩት?

**15.** አቶ ሙላቱ: እኔ…

**16.** ፖሊስ ሙሉጌታ: አቶ መኩሪያ ማነው?

**17.** አቶ ሙላቱ: **(suddenly scared)** የምክር ቤት አባሉ አቶ መኩሪያ ከዚህ ጋ የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም።

**18.** ፖሊስ ሙሉጌታ: እንደዛ ከሆነማ ለምን ባለቤትዎን ከሱ ገንዘብ እንድትቀበል ላኳት?

**19.** አቶ ሙላቱ: **(realizes)** ያደረኩትን የስልክ ጥሪ ሰምተዋል ማለት ነው? ለመሆኑ ይህ ህጉ ይፈቅዳል?

**20.** ፖሊስ ሙሉጌታ: ነግሬዎታለሁ። እዚህ ምንም አይነት መብት የለዎትም። ቢያንስ እውነቱን እስኪነግሩን ድረስ።

**21. MUSICAL INTERLUDE (tense music)**

**SCENE 2: ወ/ሮ ሉሊት AT THE አቶ መኩሪያS’**

**22. ATMO: QUIET NEIGHBOURHOOD IN THE EVENING; CRICKETS**

**23.** ወ/ሮ ሉሊት: **(to herself)** አሀ! አቶ መኩሪያ የሚኖረው እዚህ ነው ማለት ነው። አቤት! ቤቱ እንዴት ትልቅ ነው።

**24. SFX: DOG GROWLS AND BARKS MENACINGLY**

**25.** ወ/ሮ ሉሊት: **(screams)** ኡ ኡ ኡ ! ኧረ ውሻው፣ ውሻው ሊገለኝ ነው። ድረሱልኝ።

**26. SFX: STEPS AS አቶ መኩሪያ APPROACHES**

**27.** አቶ መኩሪያ: **(to the dog)** ሣልሳዊ ፤ አንተ ውሻ እረፍ ብዬሀለሁ።

**28. SFX: DOG WHINES AND STOPS BARKING**

**29.** አቶ መኩሪያ: **(to ወ/ሮ ሉሊት)** እድለኛ ነሽ። በአጋጣሚ እኔም ወደ ውጪ እየወጣሁ ባይሆን ኖሮ ሣልሳዊ ቦጫጭቅሽ ነበር። ማን ነሽ ለመሆኑ?

**30.** ወ/ሮ ሉሊት: **(still out of breath)** ሉሊት እባላለሁ የአቶ ሙላቱ ባለቤት ነኝ። እርሶን እንዳገኝ ልኮኝ ነው።

**31.** አቶ መኩሪያ: **(angry)** ይህ አጭበርባሪ ከኔ ምን ፈልጎ ነው?

**32.** ወ/ሮ ሉሊት: ሙላቱን አሰረውታል።

**33.** አቶ መኩሪያ: **(interested)** አሰረውታል? እውነትሽን ነው? ለምን ተብሎ? ግቢ - ውስጥ ብናወራ ይሻላል።

**34. SFX: GATE/DOOR BEING OPENED**

**35. SFX: FOOTSTEPS AS THEY ENTER**

**36.** አቶ መኩሪያ: ተቀመጭ

**37. SFX: CLOTHES RUSTLING AS THEY SIT**

**38.** አቶ መኩሪያ: አሁን ባለቤትሽን ለምን እንዳሰሩት ንገሪኝ

**39.** ወ/ሮ ሉሊት: **(hesitates)** የበፊት አለቃውን የሆነ ሰው ዘርፎታል።

**40.** አቶ መኩሪያ: **(pleased)** አሀ…

**41.** ወ/ሮ ሉሊት: **(firm)** ይጠረጥሩታል። ግን እሱ ሌባው አይደለም።

**42.** አቶ መኩሪያ: እና ወደዚህ የመጣሽው ይህን ብቻ ልትነግሪኝ ነው?

**43.** ወ/ሮ ሉሊት: **(hesitates)** አይደለም… ልጆቹ ተርበዋል የምንበላው የለንም። እና ለባለቤቴ ስነግረው እሱ ይረዳሻል ብሎኝ ነው ወደ እርስዎ የመጣሁት።

**44. SFX: FIST BANGING ON TABLE**

**45.** አቶ መኩሪያ: **(getting angry)** ስሚ! ስለ ህፃኗ ከሆነ የተጠየኩትን ክፍያ ሰጥቻለሁ። ጠቅላላ ገንዘቡን ከፍየዋለሁ። እናንተ ሰዎች ለምን እንደማይገባችሁ አላውቅም። ውል ውል ነው።

**46.** ወ/ሮ ሉሊት: **(confused)** ህፃኗ? የምን ህፃን ነው?

**47.** አቶ መኩሪያ: ያመጣልኝን ህፃን ነዋ… እ... **(realises he has let the cat out of the bag)** ስለ ህፃኗ የማውቀው ነገር የለም እንዳትይኝ።

**48. SFX: ወ/ሮ ሉሊት GETS UP**

**49. ወ/ሮ ሉሊት:** ሙላቱ ልጄን የሸጠለት ሰው አንተ ነህ? **(frantic)** ልጄን መልሰህ ስጠኝ። ልጄን መልስ ብዬሀለሁ!**(continues to scream)**

**50. አቶ መኩሪያ:** **(harshly)** ስሚ! ይህ ቀላል የማይባል ገንዘብ ነው ለህፃኗ የከፈልኩት። በዛ ላይ ያሉሽን ልጆች እንኳን የምታበያቸው የለሽም።

**51. SFX: RUSTLING OF CLOTHES AS ወ/ሮ ሉሊት ATTACKS አቶ መኩሪያ**

**52. አቶ መኩሪያ:** በይ ሂጂ ጥፊ ከዚህ አሁን

***KW BEGIN***

**53. ወ/ሮ ሉሊት:** **(goes berserk)** ልጄን ስጠኝ ብያለሁ።

**54. አቶ መኩሪያ:** **(trying to calm her)** ስሚ! የተወሰነ ገንዘብ እሰጥሻለሁ። ይህ ግን ለመጨረሻ ጊዜ ነው።

**55. SFX: BILLS BEING COUNTED**

**56. ወ/ሮ ሉሊት:** ገንዘብህን አልፈልግም ልጄን ብቻ መልስልኝ።

***KW END***

**57. SFX: BABY CRYING IN ANOTHER ROOM**

**58. ወ/ሮ ሉሊት:** እሷ ናት? ወይኔ ልጄ! የኔ ልጅ

**59. SFX: አቶ መኩሪያ GRABS ወ/ሮ ሉሊት AND DRAGS HER TOWARDS THE DOOR**

**60. SFX: DOOR OPENS**

**61.** አቶ መኩሪያ: **(threatening)** ሂጂ ውጪ። ሁለተኛ ድርሽአላለሁ ብትይ ውሻውን ሣልሳዊን ነው የምለቅብሽ። ስለእዚህ ጉዳይ ደግሞ ጨርሶ ከሰው ጋ ለማውራት እንዳትሞክሪ።

**62. SFX: DOOR BEING SLAMMED**

**63. SFX: ወ/ሮ ሉሊት BANGS AGAINST THE DOOR**

**64.** ወ/ሮ ሉሊት: **(screams desperately)** ልጄን እፈልጋታለሁ።

**65. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ንጉሴ DECLARES LOVE TO AN OLD WOMAN</u>**

**66. ATMO: STREET ATMO, LIGHT TRAFFIC, AT NIGHT**

**67. SFX: RAIN AND THUNDER**

**68. SFX: DRUNKEN FOOTSTEPS ON WET GROUND**

**69.** ንጉሴ: **(drunk tone: he is practising his words)**

"እኔ ንጉሴ ጃለታ ምህረት ሙላቱን አፈቅራታለሁ። ምህረት እኔ እንደማፈቅርሽ ግን ለምንድን ነው የማታፈቅሪኝ? ከዳንኤል ጋ ጉዳይ የነበርሽ ቢሆንም ደንታ  አይመስለኝም። ለማንኛውም አፈቅርሻለሁ።! በቃ! እንደዚህ ብዬ ነው የምነግራት። ወየው ይሄ ነው ቤቷ!

**70. SFX: FOOTSTEPS STOP**

71. ንጉሴ: **(calls out)** ምህረት መስኮቱን ክፈቺው!

**(to himself)** ውይ - መብራቱን አበራችው!

**(shouts)** እኔ ነኝ! ንጉሴ! አበባ ይዤልሽ መጥቼያለሁ። የኔ ቆንጆ የኔ ንግስት!

**72. SFX: STEPS APPROACHING ON WET GROUND**

73. ትዕግስት: ንጉሴ? ምን እያደረክ ነው?

74. ንጉሴ: አ ትዕግስት! የኔ ጓደኛ እና የክፍሌ ልጅ ትዕግስት! እስቲ እቀፊኝ።

**75. SFX: CLOTHES RUSTLING AS THEY HUG**

76. ትዕግስት: ጋን ጋን ትሸታለህ **(disgusted)** ንጉሴ ሰክርሃል እንዴ? ከመቼ ጀምሮ ነው ደግሞ መጠጣት የጀመርከው?

77. ንጉሴ: ልታናግረኝ እንኳን ከማትፈቅደው  ልጅ ፍቅር ይዞኛል።

***KW BEGIN***

78. ትዕግስት: ከየትኛዋ ልጅ? ከምህረት መስሎኝ ፍቅር የያዘህ?

79. ንጉሴ: አዎ ከምህረት ነው! ደግሞ እሷም ለኔ የሆነ ስሜት እንዳላት አውቃለሁ። ከአይኗ ማንበብ እችላለሁ።

***KW END***

**80.** ትዕግስት: ኡኡኡ እንዴት ያለ ፍቅር ነው! ግን የምህረት ቤተሰብ ተመልሶ ወደ ታንዲካ ጎስቋላ መንደር እንደገባ አታውቅም?

**81.** ንጉሴ: ምን? ሂጅ ውሸታም።

**82. SFX: WINDOW OPENS**

**83. OLD WOMAN:** **(from afar)** ውይ የኔ ቆንጆ ወጣቱ መርከበኛ! እኔም አፈቅርሃለሁ። ጠብቀኝ የኔ የምስጥር ወዳጅ። ጠብቀኝ እየመጣሁ ነው።

**84. SFX: WINDOW CLOSED**

**85.** ትዕግስት: ሃ ሃ ሃ! ይሄው ማረጋገጫው !

**86.** ንጉሴ: **(panics)** የፈጣሪ ያለ። ከዚህ መጥፋት አለብኝ

**87. SFX: STEPS ON WET GROUND RUNNING AWAY**

**88.** ትዕግስት: **(calling after him)** ስማ አንተ ቆንጆ ሰካራም መርከበኛ። ቢያንስ እንኳን ለምን አበቦቹን አትተውላትም? **(laughs)**

**89. SFX: DOOR OPENS**

**90. OLD WOMAN:** **(calling)** ጠብቀኝ እረ ቁም ወዴት ነው የምትሄደው?

## SCENE 4: ምህረት VISITS ዳንኤል AT NIGHT

**91. ATMO: DORMITORY AT NIGHT**

**92. SFX: STEPS ምህረት**

**93. ምህረት:** **(to herself)** መጠንቀቅ አለብኝ። እድለኛ ነኝ ዘበኛው ተኝቷል። ያለዚያ ማ! በዚህ በሌሊት በፍፁም ወደ ወንዶች ማደሪያ መግባት አልችልም ነበር።

**94. SFX: STEPS STOP**

**95. ምህረት:** **(takes a deep breath)** ይኼው ደረስኩ።

**96. SFX: KNOCK ON DOOR**

**97. ዳንኤል:** **(sleepily, from inside)** ማነው?

**98. ምህረት:** **(whispers)** ዳንኤል፤ ምህረት ነኝ። እባክህ በሩን ክፈተው።

**SILENCE**

**99. ምህረት:** ዳንኤል?

**100. SFX: FOOTSTEPS ዳንኤል APPROACHING FROM INSIDE**

**101. SFX: DOOR OPENS**

**102. ዳንኤል:** **(annoyed)** ምህረት ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት እዚህ ምን ታደርጊያለሽ?

**103. ምህረት:** **(whispers)** እባክህ እንድገባ ፍቀድልኝ

**104.** ዳንኤል: ምን ፈልገሽ ነው ምህረት?ምንም ይሁን ምን አፍጥኚው እና ከዚህ ሂጂ።

**105. SFX: ምህረት’S FOOTSTEPS ENTERING**

**106. SFX: DOOR CLOSES**

**107.** ምህረት: **(breaks down)** በፍቅርሽ አበድኩኝ ስትል አልነበር። ታድያ አሁን ምን ሆንክ?

**108.** ዳንኤል: **(coldly)** ምንም የሆንኩት ነገር የለም። አንቺ ግን በርግጠኝነት የሆነ ነገር ሆነሻል። ላላደረጉት ነገር ደግሞ ምንም አይነት ኋላፊነት አልወስድም።

**109.** ምህረት: አባቱ አንተ ነህ። ከአንተ ውጪ ከማንም ጋ አልተኛሁም።

***KW BEGIN***

**110.** ዳንኤል: እሱን በምን አውቃለሁ?

**111.** ምህረት: ዳንኤል አብረን ስንተኛ ድንግል እንደነበርኩ ታውቃለህ። ከዚህ ሌላ ምን አይነት ማረጋገጫ ነው የምትፈልገው? በፍፁም እንደማትተወኝ ደግሞ ቃል ገብተህልኝ ነበር።

**112.** ዳንኤል: ያ ማ! ከሌሎች ወንዶች ጋ አብረሽ መተኛት ከመጀመርሽና እኔን አስረገዝከኝ ብለሽ መውቀስ ከመጀመርሽ በፊት ነው።

**113.** ምህረት: **(shocked)** እንዴት - እንዴት እንደዚህ ልትል ትችላለህ?

***KW END***

**114.** ዳንኤል: ምህረት ይህን ነገር ማስወጣት አለብሽ።

**115.** ምህረት: አይሆንም ዳንኤል ። ስለልጁ አስብበት - የኛ ልጅ። ከባድ እንደሆነ ይገባኛል። ግን በአንድነት እንወጣዋለን።

**116.** ዳንኤል: **(aggressively)** ሂጅ ውጭ ከዚህ ካለበዚያ ዘበኛውን እጠራዋለሁ!

**117.** ምህረት: ግን ይህንንም ቢሆን ብቻዬን አልወጣውም። ፅንሱን ለማስወረጃ …እንኳን የሚሆን ገንዘብ የለኝም።!

**118.** ዳንኤል: ውጭ ከዚህ

**119. SFX: STRUGGLE AS SHE IS PUSHED OUT**

**120. SFX: DOOR CLOSED**

**121. SFX: DOOR HIT**

**122.** ምህረት: **(hits door and cries)** እባክህ ዳኒ እረፍ። እንደዚህ አታድርግ።

**123. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

ለዛሬ ያልነው የበማድመጥ መማር ጭውውት የእስካሁኑ ነበር። ዳንኤል ለምህረት ሊላት የሚችለው ይህንብቻ ይሆን? የሚቀጥለው ክፍል እንዳያመልጣችሁ። ይህንን እና ሌሎች ክፍሎችን ደግማችሁ መስማት ከፈለጋችሁ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን ጎብኙ፤ እዛም ላይ አዲስ የበማድመጥ መማር የቪዲዮ ዘገባ ይጠብቃችኋል። "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ »ን በተመለከተ ለየት ባለ መልኩ የተቀናበረ ነው። ይህ ብቻም አይደለም፤ የዳንኤል የተለየ አመለካከትም አለበት። አስታውሱ በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ስለሰማችሁት መዋያየት ትችላላችሁ። እስከሚቀጥለዉ ጊዜ፤ ጤና ይስጥልን።